ፊት ለፊት የማስተርጎም አገልግሎቶች

የ ACPS እንቅስቃሴን ላይ ሲካፈሉ ወይም የልጅዎ ትምህርት ቤት ስብሰባ ወቅት አስተርጓሚዎቻችን የ ACPS ቤተሰቦችን ለመርዳት ዝግጁ ናቸው።

ይህን አገልግሎት ለመጠየቅ፣ እባክዎን አገልግሎቱ መኖሩን ለማረጋገጥ የልጅዎን ት/ቤት ከ 5 የትምህርት ቀናት በላይ አስቀድመው ያስታውቁ።

አስተርጓሚዎች ለወላጅ መምህር ጉባኤዎች፣ የልጅ ግምገማ ስብሰባዎች፣ የልዩ ትምህርት ብቁነት ስብሰባዎች እና የልዩ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባዎች ለመሳሰሉት የተለያዩ ስብሰባዎች አስተርጓሚዎች ሊቀርቡ ይችላሉ። አስተርጓሚዎች በወርክሾፖች፣ በወላጆችና መምህራን ማህበር (PTA) ስብሰባዎች፣ በእንደገና-ወደ-ት/ቤት መመለሻ ምሽቶች በመሳሰሉ እና ሌሎችም የት/ቤት እንቅስቃሴዎች ወቅት ሊረዱም ይችላሉ።

የጽሁፍ ትርጉም አገልግሎቶች

ACPS የትምህርት ቤት እና የወላጆችን ግንኙነት ለማገዝ በመላው ክፍሎች ያሉ ሰነዶችን ይተረጉማል። እነኚህ ሰነዶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ በነዚህ ግን አይወሰኑም፡- የክፍል እና የትምህርት ቤት ፖሊሲዎች፣ የአደጋ ጊዜ መረጃ፣ የምዝገባ እና የምደባ ቅጾች፣ የጤና እና የደህንነት መረጃ፣ የተማሪ ፍቃድ ቅጾች፣ የስነ-ምግባር ደብዳቤዎች፣ የወላጅ መመሪያ መጽሃፍ እና የመረጃ ወረቀቶች፣ የትምህርት አማራጮች እና እቅዶች፣ የትምህርት-ነክ እንቅስቃ ሴዎች ወይም ተግባራት፣ የሪፖርት ካርዶች እና የፕሮግራም ተኮር መረጃ ተደራሽነትን የተመለከተ መረጃ።

አንድ እንዲረዱት እርዳታ የሚያስፈልግዎ ሰነድ ካለ፣ ይህን የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ እንዲያውቅ ያድርጉ።

ለተጨማሪ መረጃ

በሚከተለው ያግኙን፡-

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ጽህፈት ቤት አገልግሎቶች
የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

ACPS ማዕከላዊ ጽ/ቤት
1340 Braddock Place
703-619-8347
www.acps.k12.va.us/translation

FACE ማእከል

ACPS ማዕከላዊ ጽ/ቤት
1340 Braddock Place
703-619-8055
www.acps.k12.va.us/face

ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች አልዎት? ድጋፍ ይፈልጋሉ?

ማንኛውም ጥያቄዎች ካልዎት ወይም አስተርጓሚ ወይም ተርጓሚ ለማግኘት ከፈለጉ፣ የ ACPS ሰራተኛን እንዲረዳዎ ይጠይቁ።

Alexandria City Public Schools

የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

ለ ACPS ቤተሰቦች ይገኛሉ

የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶች አጠቃላይ እይታ

ከ 50% በላይ የሚሆኑት የአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች እቤት ውስጥ ከእንግሊዝኛ ሌላ አንድ ቋንቋ ይናገራሉ። በ ACPS ተማሪዎች መካከል በብዛት የሚነገሩት ቋንቋዎች ስፓኒሽ፣ አማርኛ እና አረብኛ ናቸው።

በትምህርት ቤቶች፣ በተማሪዎች እና በቤተሰቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ለማገዝ የ ACPS የቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ በቴሌፎን ማስተርጎም (በ Language Line በኩል)፣ የፊት ለፊት ማስተርጎም እና የጹሁፍ ትርጉም አገልግሎቶች።

አዘውትረው ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር መገናኘት የልጅዎን ትምህርት የሚያግዙበት ወሳኝ መንገድ ነው።

አገልግሎቶችን ማግኘት

የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎት እንደሚፈልጉ ለ ACPS ሰራተኛ የሚነግሩበት የተለያዩ መንገዶች አሉ፦

- በ ACPS ልጅዎን በሚያስመዘግቡበት ጊዜ፣ ሰራተኛው (ሬጂስትራሩ) የእርስዎን ተመራጭ የግንኙነት ቋንቋ እንዲያውቅ ያድርጉ።
- በ ACPS ትምህርት ቤት ወይም ጽህፈት ቤት ከሆኑ "የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ይገኛሉ" የሚለውን ፖስተር ይፈልጉ። ከዚያም፣ ወደ ቋንቋዎ ይጠቁሙና አንድ የ ACPS ሰራተኛ አስተርጓሚውን በስልክ ያገኝዋል።

- የእርስዎ ቋንቋ በፖስተሩ ላይ ከሌለ፣ ከ100 በላይ ቋንቋዎችን የሚያካትተውን "የቋንቋ መለያ መመሪያ" ይጠይቁ።

በ Language Line በኩል የሚሰጡ የማስተርጎም አገልግሎቶች

Language Line (የቋንቋ መስመር) ከአንድ በላይ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች ከልጆቻቸው ት/ቤት ጋር የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በመጠቀም ባህላቸውን በተከተለ መልኩ በቴሌፎን እንዲገናኙ የሚያስችል አገልግሎት ነው።

የልጅዎ ትምህርት ቤት፣ Language Line በመጠቀም በስልክ አስተርጓሚ መጥራት ይችላል። የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ የ Language Line ቁጥሩን ይደውልና የሚፈለገውን ቋንቋ ይጠይቃል። ከዚያም እርስዎ አስተርጓሚው እስኪገናኝ በመስመር ላይ ሆነው መጠበቅ ይኖርብዎታል፣ በአብዛኛው ከ 1-2 ደቂቃዎች።